## 4. ኢኮኖሚውን መልሶ ለማቋቋም አስቸኳይ እርምጃዎች፣

### 4. 1. የፖላንድ ምሳሌ፣

ወይዘሮ ማርያ ኖዋክ
/ፓሪስ ፈረንሳይ/

ከዓለም ባንክና ከአውሮፓ የጋራ ገበያ ኤክስፐርቶች ጋር በመተባበር ከአንድ ዓመት ወዲህ ስለ ፖላንድ ኢኮኖሚ ጥናት በማድረግ ላይ ነኝ፡፡ምንም እንኳን ነገሮችን ከውጭ የምከታተል ቢሆንም የፖላንድ ተወላጅ በመሆኔ ሙሉ በሙሉ ገለልተኛ ሆኜ አላያቸውም፡፡

ከሁሉ አስቀድሜ የኮሚኒስት አገዛዝ የፖላንድን እርሻ እንዴት እንዳወደመው ለማሳየት አንድ ምሳሌ መጥቀስ እወዳለሁ፡፡ በ1909 ዓ.ም. የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች 21 ሚሊዮን ቶን እህል ለውጭ ገበያ ያቀርቡ ነበር፡፡ በ1988 ደግሞ እነዚሁ ደገሮች ከውጭ ገበያ 32 ሚሊዮን ቶን የሚገዙበት ደረጃ ደረሱ፡፡ በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የእህል ጎተራ የነበሩት አገሮች ዛሬ ሸማቾች ሆነዋል ማለት ነው፡፡

በ1989 ዓ.ም. ማገባደጃ ላይ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ ሽግግር ፕሮግራም ከሥራ ላይ መዋል ሲጀምር ኢንፍሌሽን ከ100% በላይ ነበር፡፡ በነፍስ ወከፍ ገቢ በ1978 ዓ.ም. ከነበረው በታች ነበር፡፡ እየተከማቸ የመጣው የሃገሪቱ የውጭ እዳ ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርቷ 80% ሲሆን ለዚህ የውጭ እዳ ይከፈል የነበረው ወለድ ፖላንድ ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ 5 እጅ የሚበልጥ ነበር፡፡

ኢኮኖሚው እጅግ በጠበቀ ማእከላዊ አመራር የሚንቀሳቀስ ቢሆን የምርት ኃይሎች ተውተብትበው የተያዙበት ሁኔታ ላይ ነበረ፡፡ በ1981 ዓ.ም. በወዛደር ቁጥጥር ኮሚቴዎች ከፍተኛ ሥልጣን በመሰጠቱ ከመሃል በኩባንያዎች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ላላ ያለ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመሃል ለነዚህ ፋብሪካዎች የሚሰጠው ድጎማ ከዓመት ዓመት እያደገ ሄደ እንጂ አልቀነሰም፡፡

እንግዲህ በዚህሁኔታ ነው የኢኮኖሚው የሽግግር ፕሮግራም ከሥራ ላይ መዋል የጀመረው፡፡ በመጀመሪያ ከመንግሥት በጀት በድጎማ እየተባለ ለፋብሪካዎች የሚሰጠውን ድጎማ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ተበጀ፡፡ በዚህ የተነሳ ድጎማ በማጋበስ ብቻ ይንቀሳቀሱ የነበሩት የመንግሥት ኩባንያዎች ወደ መክሰር አመሩ፡፡ ትርፍ የሆኑ ሠራተኞች በገፍ እንዲባረሩ ሲደረግ፣ እነዚህ አዳዲስ ሥራ አጦች አነስተኛም ቢሆን የኑሮ ዋስትና የሚያገኙበት ዘዴ ከሽግግር ፕሮግራሙ ጋር አብሮ ቀረበ፡፡

ከጃንዋሪ 1,1990ዓ.ም.ሌላ የሁለተኛ ሪፎርም ዙር ተጀመረ፡፡ የፖላንድ ገንዘብ የምንዛሪ ተመን ተቀነሰ፡፡ የመንግሥት ወጭ ተቀነሰ፡፡ ባንኮች የሚሰጡት ብድር ላይ ቁጥጥርና በያለበት የሚከፈሉ ደመወዞች ለተወሰነ ጊዜ ባሉበት እንዲረጉ ተደረገ፡፡ ይህ ፖሊቲካ አንዳንድ ውጤቶችን አስገኘ፡፡ከነዚህ መልካም ውጤቶች ውስጥ የዋጋ መናር መቀነስ አንዱና የመጀመሪያው ሆኖ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡ ከጃንዋሪ 1991 እስከ ሜይ ወር1991 ባለው ጊዜ ውስጥ የዋጋ መናር/ኢንፍሌሽን/ ከ79% ወደ 5% አሽቆለቆለ፡፡ በተጨማሪ የወለድ ተመን ተቀነሰ፣ የመንግሥት በጀት ከኪሣራ ወጥቶ ከ1% እስከ 3% ትርፍ አሳየ፡፡ በመጨረሻም ሃገሪቱ ከውጭ የምታስገባቸው እቃዎች መቀነስ ሲጀምሩ ለውጭ ገበያ የምታቀርባቸው እቃዎች መጨመር ጀመሩ፡፡

ይህም ሆኖ ይህ ፕሮግራም አስከፊ ውጤቶችም ነበሩት፡፡ ደመወዝ በ3 ወር በአጠቃላይና በአማካኝ 40% ያህል ቀነሰ፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለው ኢኮኖሚ ክፍል የሚያስገኘው ምርት 30% ወረደ፡፡ ቤተሰቦች ለምግብ የሚያወጡት ወጭ በኃይል ሲጨምር ከህዝቡ 30% ያህል "ዝቅተኛው የድህነት ደረጃ" ከሚባለውም መለኪያ በታች ወረደ፡፡

በእርሻው ዘርፍ መንግሥት የቀየሰው የዋጋ ትመና ፖሊሲ በአንድ ከገል አምራቾች አወንታዊ መልስ ያገኛል በሌላ በኩል ደግሞ የእርሻ ምርት ዋጋ መጨመር በገበያ ላይ እህልና ልዩ ልዩ የእርሻ ውጤቶች በሰፊው እንዲቀርቡ ያደርጋል ተብሎ ተጠብቆ ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ እንዲያውም ፖላንድ የእርሻ ምርት ለውጭ ገበያም የምታቀርብበት ደረጃ ትደርሳለች ተብሎ ነበር፡፡ ግን እንደተጠበቀው አልሆነም የፖላንድ የእርሻ ዘርፍ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ቀውስ ውስጥ ገባ፡፡ከእህል እጥረት በድንገት ወደ ምርት መትረፍረፍ ሲታለፍ የገበያው ማከፋፈያ ዘዴዎች ተናጉ፡፡ የኢኮኖሚ ሽግግሩም ፕሮግራም አንደገና ከጥያቄ ውስጥ ገባ፡፡

ይህ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ የሚደረገው የሽግግር ጥረት አስቸጋሪ የሆነው ባለፈው ሥርዓት ሥር በተሠራቁ ስህተቶች ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እስከ 1989 ዓ.ም. ድረስም ቢሆን የፖላንድ የእርሻ ዘርፍ አብዛኛው ክፍል በግል አራሾች እጅ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ለማምረትም ሆነ ምርትን ገበያ ለማቅረብ በመንግሥት ቁጥጥርና ህብረት ሥራ ማህበራት ሥር ሳለው ክፍል ጥገኛ ሆኖ የሚንቀሳቀስ ዘርፍ ነበር፡፡

እዚህ ላይ አንዳንድ ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል በቀድሞው አገዛዝ ሥር በ14.4 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የሚሠሩ 2.7 ሚሊዮን የግል እርሻዎች በ4.1 ሚሊዮን ሄክታር ላይ 1300 የመንግሥት እርሻዎችና በ400 ሺህ ሄክታር ላይ የሚሠሩ 8000 የህብረት እርሻዎች ነበሩ፡፡ትናንሽ ገበሬዎች እንኳን እርዳታ ሊደረግላቸው ቀርቶ እንዲያውም በከፋ ዓይን የሚታዩ ነበሩ፡፡ አገዛዙ ሥራቸውን በተለያዩ ዘዴዎች ለማደናቀፍ ይጥር ነበር፡፡

እንግዲህ በመንግሥት እንክብካቤ አማካኝነት ይንቀሳቀስ የነበረው የእርሻ ዘርፍ በአዲሱ ፖለቲካ ምክንያት ችግር ውስጥ ወደቀ፡፡ ለእርሻው ዘርፍ እንክብካቤ ሲባል ቀደም ሲል ከሃገሪቱ ጠቅላላ ብሄራዊ ምርት 4% ለሱው ድጎማ ይውል ነበር፡፡ አሁን ይህ ወደ0.2% ወረደ፡፡ ለውጭ ገበያ ለሚቀርበው እህል ይሰጥ የነበረው ድጎማም ሙሉ በሙሉ ተሰረዘ፡፡

የሃገሪቱ የውስጥ ገበያ እንቅስቃሴ በኃይል ቀነሰ፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ህዝቡ ገበያ ላይ ያገኘውን ሁሉ እየገዛ ያስቀምጥ ነበር፡፡ አሁን የእርሻ ምርት ስለሚገኝ አገበስብስ የመግዛት ልምድ እየቀረ ሄደ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ጊዜ በወር እስከ 40% የሚደርሰው የወለድ መጠን እጅግ ከባድ በመሆኑ ገበሬዎች ምርቶችን ሁሉ በአስቸኳይ ሸጠው ብድራቸውን ለመክፈል ይፈልጋሉ፡፡ ግን ይህም ሆኖ ገበሬዎች በሚያመቻቸው ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ ስለሌለ የ1989 ዓ.ም. ምርታቸውን ወደ ገበያ ከማውጣት ተቆጠቡ፡፡

እንግዲህ ወደ መደምደሚያ ለምጣና በሶስት መፈክሮች አማካይነት ሃሳቤን ላቅርብ።

መጀመሪያ ያለገበያ የገበያ ኢኮኖሚ የለም። የጠገገረ ፕሮግራም ለዚህ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ትኩረት አለመስጠቱ ከድክመቶቹ አንዱ ነው እላለሁ። የመንግሥትን ሞኖፖል በመስበር ብቻ ገበያ "አውቶማቲካሊ" አይፈጠርም። የኸ የገበያ መፈጠር ጉዳይ በጣም ዝግ ያለ ሂደት ነው። ምርት ወደገበያ የሚያቀርቡ ተቋሞች ሙሉ በሙሉ መቀየር አለባቸው። በውጭ ግንኙነት በኩል ደግሞ የፖላንድ ኢኮኖሚ በአውሮጳ የጋራ ገበያ ጋር ቀስ በቀስ ግንኙነቷን ማዳበር ይኖርባታል። ከምእራብ አገሮች ጋር በመደራደር በተለይ እንደፈረንሳይና ጀርመኒ ዓይነት አገሮች ለገበሬያቻቸው በሚለግሱት ድጎማ አማካኝነት የእርሻ ምርቶቻቸውን በአለባሌ ዋጋ ፖላንድ ገበያ ማፍሰሳቸውን ማገድ ያስፈልጋል። በዚህ አኳያ ደግሞ የፖላንድ የእርሻ ምርቶች በጥራታቸው በውጭ ገበያ ተፈላጊነት እንዲኖራቸው መጣር ያስፈልጋል።

ሌላው መፈክር ያለ ካፒታል ካፒታሊዝም ሊኖር አይችልም የሚለው ነው። ይኸ አነጋገር ላይ ላዩን ሲያዩት በጣም ግልጽና ቀላል ይመስላል። ግን በጣም ብዙ ችግሮች አሉ። ሁሉም ነገር ገና በተዝረከረከበት አገር እንዴት ተብሎ ከውጭ ካፒታሊስቶች ጋር "ጆይንት ቬንቸር" ሊታሰብ ይቻላል? የምእራብ ካፒታሊስቶች ፖላንድ ሲመጡ በሃገራቸው የለመዷቸውን አገልግሎቶች ለምሳሌ ቴሌፎን እንደ ልብ አያገኙም። ተስፋ ይቆርጣሉ።

የመጨረሻም መፈክሬ ሥራ ወይም ኩባንያ በሙያው የሠለጠኑ አሠሪያች ወይም "ማኔጀርስ" ይጠይቃል። ይህንን ችግር ለመወጣትና ብዙ ባለሙያዎች ለማሰልጠን የውጭ እርዳታ ያስፈልጋል፡ ችግሩ የሥልጠና ችግር ብቻ አይደለም፤ የአስተሳሰብም ለውጥ በጣም አስፈላጊ ነው። የኮሚኒስቶ አገዛዝ ጨርሶ የደመሰሰው የግል አነሳሽነትና የሃላፊነት መንፈስ ቀስ በቀስ መገንባት ይኖርበታል። በፖላንድ አንድ የተለመደ አነጋገር ነበር "ተኝቼም ቆሜም ደመወዜን አገናለሁ" በዚህ ዓይነት ሰው መሥራትና መጣርን ጨርሶ ትቷል። ይኸ ሁሉ እንደገና ካልተገነባ ሃገሪቱ መራመድ አትችልም። በመጨረሻም ሥራና አሠሪ ተገናኝተው የሃገር ልማት እንዲከተል የተረጋጋ አካባቢ የግድ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።

## 2. የዩጋንዳ ምሳሌ፤

### የዶክተር ዊሊ ካቤሩካ – በዩጋንዳ የፕሬዚዳንቱ ጽ/ቤት የኢኮኖሚ ጉዳይ አማካሪ ገለጻ

በ1986 ዓ.ም. በዩጋንዳ የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ የፕሬዚዳንቱ የኢኮኖሚ አማካሪ ሆኜ ተሾምኩ። በዚህ ሁኔታ ነው ሃገሪቱን መልሶ ለማቋቋም በተደረገው ጥረት ተሳታፊ የሆንኩት።

ዩጋንዳ ነጻ ከወጣችበት ወቅት አንስቶ አራት መንግሥታት ተፈራርቀዋል። ከ1962 እስከ 1971 ዓ.ም. የሚልተን ኦቦቴ መንግሥት፤ ከ1971 እስከ 1979 ዓ.ም. የአሚን ዳዳ መንግሥት፤ ከ1982ዓ.ም. እስከ 1985 ዓ.ም. እንደገና የሚልተን ኦቦቴ መንግሥት፤ ከጃንዋሪ 1986 ዓ.ም.ጀምሮ ደግሞ በብሄራዊ አርበኝነት ንቅናቄ የሚመራ መንግሥት።

የሀገራችንን ኢኮኖሚ አስተዳደርና ችግሮች ለማጤን ከፈለግን ታሪኳን መለስ ብለን ማየት ይኖርብናል። ቅኝ ገዥዎች ከመምጣታቸው በፊት ሃገሪቱን ከፋፍለው የሚገዙ የተለያዩ

ንጉሶችና ባላባቶች ነበሩ:: በ1893 ዓ.ም. እንግሊዞች ዩጋንዳን በቀኝ ግዛትነት ሲይዙ እነዚህ መሪያች ስለጣናቸውን ተገፈፉ:: ከህንድ ሃገር ብዙ ሠራተኞች በማምጣት በኬንያና በዩጋንዳ መሃል ያለውን የባቡር ሃዲድ ገነቡ:: ከዚያ በኋላ ህንዶች በእርሻና በኢንዱስትሪው መስክ ተሰማሩ::

ብድር እንደልብ ስላገኙ ከኤዥያ የመጡት ዜጎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በንግድና በኢንዱስትሪው መስክ ቁልፍ ቦታዎችን ለመያዝ በቁ:: የእርሻው ክፍል ግን ለአፍሪካውያን የተተወ ነበር:: በሃገሩ ህዝብ ጥረት የሚንቀሳቀሰው የገጠር ኢኮኖሚ ደህና ይሠራ ስለነበር ጥጥና ቡና ለዓለም ገበያ በማቀረብ፣ ለሃገሩ ህዝብ የሚያስፈልገውን የእርሻ ሰብል በማምረት ሃገሪቱ አንድነቷን ጠብቃ መራመድ ቻለች:: ዛሬ ኢኮኖሚያችንን መልሰን ለማቋም ስንሞክር ከመሬት ይዞታ አንጻር ምንም ለውጥ ለማድረግ አንፈልግም::

ዩጋንዳ ነጻ በወጣችበት ጊዜ ኢኮኖሚዋ በዓመት 5% ያድግ ነበር:: የተገነባውም ጥጥና ቡና ለዓለም ገበያ በማቀረብ ላይ ነበር:: ከነዚህ ሁለት ምርቶች ብቻ ሃገሪቱ ከገቢዋ 75% ታገኝ ነበር:: በ1971 ዓ.ም. አሚን ዳዳ መፈንቀለ መንግሥት ሲያደርጉ ተቃዋሚ ኃይሎች ወደ ኬንያና ታንዛንያ ተሰደዱ:: ከዚያ ተደራጅተው ትግላቸውን ጀመሩ:: በ1972 ዓ.ም. አሚን ዳዳ ህንዶችን ከሀገሪቱ በማባረር የነሱን ንብረቶች ለዩጋንዳ ተወላጆች አከፋፈሉት:: በዚህ የተነሳም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት አገኙ::

ግን ብዙ ሳይቆይ ሰው አንድ ነገር ተገነዘበ፣ ከህንዶች የተወረሱት ፋብሪካዎችም ሆኑ የንግድ ተቋሞች የታደሉት ለፕሬዚዳንቱ ወዳጆች ብቻ ነበር:: ለማከፋፈል የተወሰደው መለኪያም የሰዎቹ ችሎታ ሳይሆን ለፕሬዚዳንቱ ያላቸው ታማኝነት መሆኑ ታወቀ:: ከዚህ ጊዜ ጀምር ችግሮች መጠራቀም ጀመሩ:: በተለይ በ1973 ዓ.ም. የእንግሊዞችን ኢንዱስትሪያች የመንግሥት ሀብት ለማድረግ አዋጅ በመውጣቱ የዩጋንዳ ብቸኝነት እየከፋ በመሄዱ በተጨማሪ ከባድ የኢኮኖሚ ችግሮች ይደራረቡባቸው ጀመር::

በዚህ ላይ እንገዲህ በተቃዋሚነት የሚጠረጠሩ ሰዎች በየቀኑ እየታፈኑ ይገደሉ ጀመር:: ችሎታ ያላቸው ዜጎች በገፍ ተሰደዱ:: የኢኮኖሚው ቀውስ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የውጭ አገሮች ለዩጋንዳ ለሚሸጡት ነገር ሁሉ የ3 ወር ቅድሚያ ክፍያ ጠየቁ:: ጥቁር ገበያና የቡና ኮንትሮባንድ ንግድ እየዳበረ መጣ::

በ1979 ዓ.ም. ይኸ ሁሉ ችግር እያለባቸው አሚን ዳዳ የታንዛንያን ሰሜን ክፍል ወረው ለመያዝ ሞከሩ:: ታንዛንያ በዚህ ምክንያት ዩጋንዳን ወርራ ተቃዋሚ ኃይሎች አሚን ዳዳን ገለብጠው ሥልጣን እንዲይዙ ረዳቻቸው:: በ1979 እና 1980 ዓ.ም. የዩጋንዳ የፖለቲካ ኃይሎች አንድ የጋራ ግንባር ፈጥረው ሃገሪቱን ከወደቀችበት የኢኮኖሚ አዘቅት ለማውጣት ሙከራ አደረጉ:: ግን የታንዛንያ ወታደሮችና አንዳንድ የዩጋንዳ ዜጎች የተጭበረበረ ምርጫ አካሂደው ሚልተን ኦቦቴ ሥልጣን እንዲይዙ አደረጉ:: ይህ ደግሞ ሌላ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ወለደ የትጥቅ ትግል ተጀመረ::

ይህ ትግል በሚካሄድባቸው ዘመናት ከ1981 እስከ 1986 ዓ.ም. የሃገሪቱን ኢኮኖሚ መልሶ ለመገንባት በሚል ዓላማ የዓለም ባንክ 1.2 ቢልዮን ዶላር ብድር ሰጠ:: ግን በዚህ ገንዘብ ምንም ሳይሰራበት ባከነ:: ዩጋንዳ ከዚህ ገንዘብ ምንም ጥቅም ባታገኝም ዛሬ አበዳሪያቻችን ከፈሉ በለው አፋጠው ይዘውናል::

በ1986 ዓ.ም. "ብሄራዊ የአርበኝነት ንቅናቄ" ሥልጣን ሲጨብጥ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ይገኝ ነበር፡፡ በሥልጣን በባለጉ ሰዎች እጅ ውስጥ ሆና ወደ ኋላ የሚራመድ ኢኮኖሚ ነበር፡፡ ከአሳ ማጥመድና ከአደን የኢኮኖሚ ዘርፎች በስተቀር ሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ በሙሉ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ የሚገኝ ነበር፡፡

ከነዚህ ችግሮች ውስጥ አንዳንዶቹን ብጠቅስ የተተረፈረፈ ቢሮክራሲ፣ ከሃገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት 13 ጊዜ እጥፍ የሆነ በጀት፣ 360% የሚጠጋ የዋጋ መናር /ኢንፍሌሽን/ አንድ ቢሊዮን ተኩል የውጭ እዳ፣ የቡና በዓለም ገበያ መውደቅ፣ የመገናኛና የአገልግሎት ተቋሞች በጦርነቱ ምክንያት የወደሙበት አገር...፡፡

ሃገሪቱን እንደገና መልሶ ለመገንባት አዲሱ መንግሥት ከሁሉ በፊት የፖለቲካ ኃይሎች በሙሉ ተሳትፎ የሚረጋገጥበትን መንገድ ማደራጀት ነበረበት፡፡ ስለሆነም በያለበትና በየደረጃው ህዝቡን ለማሳተፍ የሚያስችል "የአርበኝነት ኮሚቴዎች" የሚባሉ ተቋቋሙ፡፡ እነዚህ በወረዳ፣ በአውራጃ፣ በክፍለ ሃገርና በአገር አቀፍ ደረጃ ቀስ በቀስ ተገነቡ፡፡ በተጨማሪም የተለየ የአስተዳደር መዋቅሮችን በማቋቋም የሃገሪቱ ልማት ለየአካባቢውና በየብሄረሰቦች በተስተካከለ ሁኔታ የሚዳረስበትን፣ እንደዚሁም በጦርነት በጣም የተጎዱ አካባቢዎች መልሰው ሊያንሠራሩ የሚችሉበትን መንገድ በመተለም ሙከራ ተደረገ፡፡

ኢኮኖሚውን መልሶ ለማቋቋም የተደረገው ሙከራ በሁለት ደረጃ የሚታይ ነው፡፡ መጀመሪያ ያውም እርዳታን በማንቀሳቀስ የህዝቡን መሠረታዊ ችግሮች ማለትም የምግብ፣ የልብስ፣ የመድሃኒት ወዘተ..ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ በ1987 ዓ.ም. ዋና ዋናዎቹን የልማት አቅጣጫዎች ከተለምን በኋላ ከዓለም ባንክ ጋር መደራደር ጀመርን፡፡ ይህንን ድርድር በምናደርግበት ጊዜ ቀደም ሲል የነደፍነውን "ባለ አሥር ነጥብ ፕሮግራም"ይዘን ነው የዚህ ፕሮግራም ይዘት፦

1/ ዲሞክራሲ፣
2/ የሁሉም ዜጋ ፀጥታና የንብረት ዋስትና መከበር፣
3/ የብሄራዊ አንድነት መጠናከርና፣ የማንኛውም ዓይነት አድልዎ መወገድ፣
4/ የሀገር ነጻነትን መከላከልና መጠናከር፣
5/ ነጻና እየተጋጋዘ የሚያድግ ኢኮኖሚ መገንባት፣
6/ የፈራረሱትን የማህበራዊ አገልግሎት ተቋሞች መልሶ መገንባትና ማጠናከር፣
7/ በሥልጣን መባለግን መዋጋት፣
8/ ቀደም ሲል የተፈጸሙና የህረተሰቡን ኑሮ ያናጉትን ስህተቶችና ጠንቆች መዋጋት፣
9/ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር በመተባበር በሌሎች አፍሪካ ሃገሮች የሚገኙ ወንድሞቻችንን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መንከባከብ፣
10/ የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መከተል፣

የሚሉ ናቸው፡፡

ከዓለም ባንክ ጋር ድርድሩ ሲጀመር የ3 ዓመት "የማገገሚያ ፕሮግራም" ነበረን፡፡ በዚህ ፕሮግራም መሠረት ቅድሚያ ለመስጠት የሞከርነው የአገር ግንባታ ጥረታችንን ሊያፍኑ የሚችሉ አንዳንድ ማነቆዎችን ለማስወገድና ለመጪው መንገድ ለመጥረግ ነበር፡፡ በመሆኑም ይኸ ፕሮግራም ያተኮረው፦

1/ ለገበሬዎች የእርሻ መሣሪያ፣ ዘር፣ መድሃኒት ወዘተ ማቅረብ፣
2/ የተሰባበረ ዋና ዋናዎ ሆኑ መጋቢ መንገዶችን መልሶ መገንባት፣
3/ ከገጠር ወደ ከተማ ከከተማ ወደ ገጠር የሰመረ ንግድ እንዲኖር በተቻለ መጠን ካሚዮኖችን ማቅረብ፣
4/ ለህዝቡ እንደ ውሃ፣ ኤሌክትሪክሲቲ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማቅረብ፣
5/ ለኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃና ተለዋጭ እቃዎችን በማቅረብ፣

ለህዝቡ የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ሸቀጦች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማገዝ::

ይሸ ኘላን ከሥራ ላይ በመዋሉ አጥጋቢ ለውጦች በመገኘት ላይ ናቸው:: በ1985 ዓ.ም. የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በዓመት 5..5% ይቀንስ ነበር ከ1987 ዓ.ም. በኋላ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ እስከ ዛሬ ድርስ በዓመት በአማካኝ 5.9% እድገት ይታያል::

ከዋጋንዓ ለምዱ የምንቀስማቸው ትምህርቶች ብዙ ናቸው:: በጦርነት የወደመ ኢኮኖሚ መልሶ እንዲያገግምና እንዲዳብር ከሁሉ በፊት ሰላምና የተረጋጋ ሁኔታ ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ በህግና በዲሞክራሲ የሚሠራ መንግሥት ይጠይቃል:: እነዚህ ከሌሉ ለረዥም ጊዜ እየታቀደ ከሥራ ላይ ሊውል የሚችል ፖሊሲ አይኖርም:: ሁለተኛ የሃገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ በጥሞና በመተንተን ዋና ዋና ችግሮች ያሉባቸውን ክፍሎችና እነሱ ቢንቀሳቀሱ ሌላውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ሊያንቀሳቅሱ የሚችሉትን ክፍሎች ማጤን፣እነሱም ላይ ማተኮር ያስፈልጋል:: በመጨረሻም የሃገሪቱ የረዥም ጊዜ ዓላማ በግልጽ የተቀመጠበት ኘሮግራም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: ምክንያቱም የአጭር ጊዜውን የመልሶ መቋቋም ቀደም ተከተል ለመወሰን ይረዳናል::